


# ኢትዮጵያና ግብጽ በህዳሴው ግድብ ዙርያ

## አይነኬ፣ ተካካሽ እና የጋራ አጀንዳዎች

ዳደ ደስታ dadeyom@gmail.come ከኤርማይን ሚድያ

### 1. የድንጋይ ቅርስ - የውሃ ቅርስ

የኢትዮጵያውያን ደማቅ ታሪክና ስልጣኔ ከወረቀትና ብራና በፊት ድንጋዮች ላይ ተጽፏል። የአክሱም ሃውልቶች አሁን በአካል ቆመው ባናያቸውና በዓይን ምስክሮች ወይም በታሪክ ጸሃፍት ተጽፈው ቢነገሩን ኖሮ አናምናቸውም ነበር። እንዴት ሰሩዋቸው የሚለው አሁንም ድረስ ዕንቆቅልሽ ሆኖ ቢቀጥልም የአንድ ወቅት ገናና ስልጣኔያችን ማሳያዎች ስለመሆናቸው ግን ራሳቸውን ችለው ይናገራሉ። ። የላሊበላ ውቅር አብያተክርስትያን ተዓምረ-ትንግርትንም እንደዚሁ። ነገር ግን እነዚያ ከተዓምር የሚቆጠሩ ቅርሶች በአካል ከመካከላችን ቆመው ስለምናያቸው "እንዴት" እያልን መልስ ፍለጋ እንኳትናለን እንጂ ህላዌያቸውን መካድ አንችልም። ኢትዮጵያውያን ከአክሱም ስልጣኔ በፊት፣ የሜሶፖታምያ ስልጣኔ እንደገነቡ፣ ከዚያም ወደ ግብጽ ተሻግረው የግብጽ ፒራሚዶች ግንባታን ወደ ሌላ ወደር የለሽ የረቀቀ የስልጣኔ ሰገነት እንዳሸጋገሩት የታወቁ የታሪክ ተመራማሪዎች ጭምር በሙሉ መተማመን የሚመሰክሩት ሃቅ ሆኗል። ዞሮ ዞሮ ተረካቢ ትውልዶች የነበረውን ገናና ስልጣኔ ማስቀጠል ባለመቻላቸው ስለ ጥንት ትልቅነታችን የሚነግሩን እነዚሁ በዘለዓለማዊነት የቆሙ የድንጋይ ቅርሶቻችን ናቸው። የእውቀትና የብራና ቅርሶቻችን ተንጠባጥበው በመጥፋታቸው የስልጣኔዎቹ መፍቻ ቁልፍ ባናገኝም፣ ቤቱ ግን እንደተቆለፈም ቢሆን ሚስጥሩን ታቅፎ አብሮን አለ። ይህ ትውልድ ከረዥም እንቅልፍና ቅዠት ወደ ጤናማው ህልም እየተመለሰ ይመስላል። ህዳሴና ትንሳኤ በሚሉ የሚገለጽ የራሱን ቅርስና አሻራ በውኃ ላይ እየገነባ ነው።

የህዳሴን ግድብ ግንባታ ከተጀመረ 5ኛ ዓመት ሊደፍን 45 ቀናት ይቀራሉ። ግንባታውን ለማጠናቀቅ የሚቀረው ደግሞ 45% አካባቢ ነው። የህዳሴን ግድብ ገንብቶ መጨረስ ማለት ኃይል ማመንጨት መቻል ማለት ብቻ አይደለም። የግብጽን ድንበር ዘለል አፍራሽ እጆችንም ከኢትዮጵያ ጉዳዮች እንዲገደቡ ማድረግ ማለት ነው። ይህ የመጀመርያው ውጤት ሲሆን የኋላኋላ የኢትዮጵያና የግብጽ እጆች በወዳጅነትነት እየተጨባበጡ እንዲዘልቁ ማድረጊያም ነው። ወደ ፊት ኢትዮጵያ የግብጽ ድጋፍና አጋርነት ሳትጠይቅ የምታገኘው ገጸ-በረከት ይሆናል። እንግዲህ ኢትዮጵያ በዚህ ትልቅ ድል አፋፍ ላይ ስለመሆኗ በኢትዮጵያ መንግስት በኩል ግንዛቤው አለ ቢባል እንኳ ሁኔታውን የሚመጥን ጥንቃቄ በበታው ስለመኖሩ እስኪረጋገጥ የዜጎች ውትወታ አይቋረጥም። ይህ ማስታወሻም የዚያ ውትወታ አካል ነው።

ጠ/ሚ/ር መለስ ዜናዊ ከዓመታት በፊት የግብጽና የሳውዲ አክራሪ ወሃቢስቶችና ሰለፊስቶች የኢትዮጵያ ህልውና ላይ ዋነኛ አደጋና ስጋት እንደሚሆኑ ጠቁመውን ነበር። መፍትሄውም ግብጽ በመካከለኛ ምስራቅና በቀይ ባህር አካባቢ ያላትን የጎበዝ-አለቃ ተጽእኖ በኢትዮጵያ የበላይነት እንዲተካ ማድረግ መሆኑን ጨምር። አቶ መለስ መፍትሄ ብለው በጠቆሙት አቅጣጫ በቂ ስራ ሰርተው መሄዳቸው ሊያከራክር ቢችል ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ወደ ዚህ ግብ መዳረሻ የሚያደርስ ወሳኝ ፕሮጀክት በመሆኑ ይህንን አስጀምረው አልፈዋል። ይህ ግድብ መጀመርያ "ሚልየነም ግድብ" የሚል ስም ተስጥቶት ነበረ። ጥቂት ወራት ቆይቶ "ታላቁ የህዳሴ ግድብ" ተሰኘ። የስያሜውም ለውጥ ተገቢ ነው። እንዲያ እንዲሆን አቶ መለስ ያቀረቡት ሃሳብ እንደሆነም ይገመታል። ከሳቸው በፊትና ከሳቸው በላይ ስለኢትዮጵያ ህዳሴ የተናገረ የኢህአዴግ አመራር ብዙም አላውቅም። ግምቱ እውነት ከሆነ አቶ መለስ ከወጠኗቸውና ካስጀመሯቸው ብዙ ግዙፋን ፕሮጀክቶች የኢትዮጵያን ህዳሴ አብሳሪ ትልቅነት ክብር ያጎናጸፋት ፕሮጀክት ይህ ግድብ ሆኗል ማለት ነው።

ከዚህ በፊት ባስነበብኩት አጭር ማስታወሻ ላይ ይህ ግድብ ለኢትዮጵያ ወሳኝ ጉልበትና ኃይል መሆኑን ጠቁሜ ነበር። GERD, the Game Changer ስል የገለጽኩትም የኢትዮጵያን ሞጎሰ-ቦታ ለአንዴና ለመጨረሻ በአዎንታዊ መልኩ እንዴት እንደሚቀይረው ለማሳየት ነበር። ግድቡ እውነትም ጉልበት ነው- ምክንያቱም ኢትዮጵያ በሚገባት ጂኦፖለቲካዊ ማማ ላይ በማስቀመጥ ገንቢ ተጽእኖዋ ለማሳረፍ የሚያስችላት ትክክለኛ በታዋን ስለሚሰጣት። ግድቡ ኃይል ነው- ምክንያቱም አሁን የሚመነጨውን ድምር ኃይል ካለበት አራት እጥፍ ከፍ እንዲል ስለሚያደርገው። ስለዚህ ግድቡ ሁለት ዓይነት ፋይዳ ነው ያለው፤ የጉልበት (የተጽእኖ) እና የኃይል (ኤሌክትሪሲቲ)። ይህ ግድብ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው የላቀ ቢባልም ከዚያ በላይ ግን ዓይነተኛ መለያው ጂኦፖለቲካዊ ጥቅሙ ስለመሆኑ አያከራክርም።

በዓባይ መስመር ላይ- የህዳሴውን ጨምሮ- 4 ግድቦች ለመስራት ጥናትና ዕቅድ እንዳለ ሰምተናል። ከ4ቱ ቀድሞ የተጀመረው የመጨረሻው ትልቁ የተባለውን ነው። ምክንያቱንም ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ነግረውን ነበር፣ "ይህን ትልቁ ግድብ እንደምንም ሰርተን ከጨረስን፣ ከግብጽ ጋር የሚኖረን ውዝግብና ጭቅጭቅ ዘላቂ ምዕራፍ ያገኛል" በሚል ነበር ያብራሩት። ከትንሹ ጀምረን ወደ ትልልቆቹ ብንሄድ ግን ሁሉም ላይ ከግብጽ ጋር አታካራ መግጠማችን የማይቀር ይሆን ነበር ማለታቸው ነው። ይህ ሁኔታ በህዳሴው ግድብ ዙርያ ካሉት ገጽታዎች፣ ጂኦፖለቲካዊ ፋይዳው የፕሮጅክቱ ዋነኛ የስህበት ማዕከል መሆኑን ያሳያል። እርግጥ ኃይል በማመንጨት ለአገሪቷ ዕድገት የሚጫወተው ሚናም ቀላል አይሆንም ብለናል። እሱኛውን ግን በሁለተኛ ደረጃ የሚታይ ነው። ከዚህ ግዙፍ ግድብ መገንባት ጋር በሶስተኛ ደረጃ የሚታዩ ገጽታዎችም ይኖራሉ። ለምሳሌ ከተፈጥሮ መነካካት ጋር የሚያያዙ አካባቢያዊና ከርሰ-ምድራዊ ክስተቶችና ሁነቶች ለማለት ነው። በጥቅሉ "የጋራ" በሚል ሊገለጹ ይችላሉ።

በግድቡ ዙርያ ከታች ግርጌ ተፋሰስ ሃገሮች፣ ከግብጽና ሱዳን ጋር የሚደረጉ ድርድሮች እነዚህን ሶስት ገጽታዎች ለየብቻ ለይተው በመፈረጅ እንደየአንገብጋቢነታቸው ለኢትዮጵያ ካላቸው ትርጉም መዝነው የሚያዩ መሆን ይገባል። ይህም የድርድር ሂደትና ጥበብ አዋቂዎች "ለድርድር የማይቀርብ/ የማይሸጋሸግ ዋና ጉዳይ"፣ "ሁለተኛው ዋና ጉዳይ" እና "የማያወዛግብ ጉዳይ" ማለትም (Competitive Needs,

Redressable Needs, Mutual Needs) የሚባልቱ ዓይነት መሆኑ ነው። አሁን ጥያቄው ከህዳሴው ግድብ ገጽታዎች ውስጥ በቀጥታ የኢትዮጵያ አገራዊ ጂኦፖለቲካዊ ፋይዳዎች ከተባሉት ጋር የተቆራኙ፣ እናም በፍጹም ለድርድር መቅረብ የሌለባቸው የትኞቹ ሁኔታዎች ናቸው የሚለውን ነው። የዚህ ጥያቄ መልስ ግን ቀላል ነው። ኢትዮጵያ ከግብጽ ጋር ላላትና ተያያዥ ግንኙነቶች የተጽዕኖ ጉልበት የሚያጎናጽፏት የግድቡ ባህርያት ለይቶ መገንዘብ ነው። ይህ ግብጽ አጥብቃና በቅድሚያ የምታቀርባቸው የድርድር ጥያቄዎች ራሳቸው ወደ ተባሉት ሁኔታዎች ይጠቁማሉ።

## 2. <u>አይነኬ አጀንዳዎች</u>

አብዛኛው ጊዜ ድርድሮቹ የጦዘ መካረር ውስጥ የሚገቡት በወሳኝና ተነጣጣቂ (competitive) ባህርያት ነጥበ-ውዝግቦች ዙርያ ነው። ወሳኝ ፍልሚያ የሚካሄደውም በነዛ ጉድዮች ላይ ነው። አንዳንዴ ለማለዘቢያ ወይም እንደግርዶሽ እንዲያገለግሉ በማስለት ለመስማማት አስቸጋሪ የማይመስሉ ጥያቄዎች የሚቀርቡ ቢመስሉም ዋናው ግብ ግብ ግን ወሳኞቹ አጀንዳዎች ላይ አሸናፊ ሆኖ ለመውጣት እንደመቆናጠጫ እንዲያገለግሉ ታስበው እንጂ ወሳኞቹ አጀንዳዎች ላይ ያለበቂ ፍልሚያ የሚሸነፍ ወይም የመጀመርያ አቋሙን የሚለቅ ተደራደሪ የለም። ግብጽና ኢትዮጵያም ግድቡን ወይም በአጠቃላይ የናይልን ውኃ በተመለከተ የሚጠብቃቸው የድርድር ትንቅንቅ ኢትዮጵያ በወንዙ ላይ ያላት የቁጥጥር ጉልበትና ድርሻ ለማረጋገጥ፣ ግብጽ ደግሞ ይህ እውን እንዳይሆን በሙሉ ዓቅምና ጥበብ መታገል ነው። በዚህኛው የሞት-ሽረት አጀንዳ ላይ አሸንፎ መውጣት ለሁለቱም ያለው ትርጉም ሰፊ ነው። ግብጽ ከሞላ ጎደል ለዘመናት የቆየውን የውኃው ብቸኛ ተጠቃሚነት በአንድ በኩል፣ እንዲሁም የኢትዮጵያን የመጠቀም ፍላጎትና አቅም እንደነበረው ማስቀጠል ሲሆን ኢትዮጵያ ደግሞ ይህንን አስተሳሰብና ሁኔታ እሰከ ወዲያኛው ማስቀየር ነው። በዓለም አቀፍ ዲፕሎማሲያዊ አሻጥር፣አለያም በደህንነታዊ ሴራዎችና ወታደራዊ ዛቻዎች፣ ካልሆነም በየድርድሩ ፍልሚያ በተናጠል ወይም በጣምራ የሚገለጽ ይሁን እንጂ የትግሉ ማዕከላዊ ግብ እሚሽከረከረው አሁን በጠቀስኩት ጭብጥ ዙርያ ነው። ስለዚህ  የኢትዮጵያን በዓባይ ውኃዊ ሃብቷ ላይ የማዘዝ ዓቅሟንና መብቷን በማከላሸትና በማቃናት መካከል አገራዊ ወሳኝ ጥቅሞቻችን በውስብስብ የድርድር ሂደቶች በሚሰነቀሩ የተንኮል ቀዳዳዎች ሾልከው እንዳይጠፉብን መድረኮቹን የሚመጥን ዝርዝር እውቀትና የሃሳብ ልዕልና ታጥቀን መቅረብ አለብን።

በቅርቡ አንድ Tom Campbell  የተሰኘ ተንታኝ ምሁር ስለ ህዳሴው ግድብ ባሰራጨው ጽሁፍ እንዲህ ብሏል፤ "ይህ ግድብ የአንድ ሙሉ አገር-አቀፍ ኢትዮጵያዊ ህልምና ምኞት ማብሰርያ ፕሮጀክት ነው። የውጭ ተሳትፎና ድርሻ ያለው ፕሮጀክት አይደለም። የዓለም ባንክ ለዚህ ፕሮጀክት ፈንድ ሊያቀርብ ፈቃደኛ አልሆነም። ምክንያቱም ግብጽ የውኃ ድርሻዋን እንደሚነካባት አጠንክራ ስለሞገተች። የዓለም ባንክን በአቻ-የለሽ ድምጽ እምታሽከረክረውና ከግብጽ ጋር የጠበቀ ወዳጅነት ያላት አሜሪካ ደግሞ ከኢትዮጵያ ይልቅ የግብጽን ፍላጎትና ስጋት ታስቀድማለች። ይህንን ከብዙ ሙከራ በኋላ የተገነዘቡት ኢትዮጵያውያንም የራሳቸውን ኪስ አስተባበሩ። ለተቀረውም የቻይናን እርዳታ ጠየቁ።" ይህም ማለት ግብጽ ዓባይ ላይ በሚሰራ ግድብ ፈጽሞ ዋዛ አታውቅም። ተቃውሞዋን በእጇ ባለው የራሷ ዓቅም በሙሉ ብቻ ሳይሆን የኃያላን ወዳጆቿ ጉልበትንም በማስተባበር ግድቡ እንዳይሰራ ትታገላለች ለሚለው ማሳያ

ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያንም ቁርጠኝነት ከግብጹ የበለጠ እንጂ ያነሰ መሆን የለበትም። ይህን አይነኬ ያልነው አጀንዳ ወሳኝ የትግል ነጥብ በመሆኑ ኢትዮጵያውያን በሙሉ ልብ ለማሸነፍ ብቻ የሚሰሩበት ግንባር ነው። እዚህኛው አጀንዳ ላይ ከግብጽ ወንድሞቻችን ጋር እምንጋራው ድል የለም። እያንዳንዷ የግድቡ ስኬት ለኢትዮጵያውያን ፍስሃ የመሆኗን ያህል ለግብጾች ሌላ ስሜት ናት። ይህ ግን ይህንን ወሳኝ የግንባታ ም ዕራፍ ሙሉ በሙሉ እስኪታለፍ ነው። ከዚያ በኋላ ኢትዮጵያና ግብጽ በግድቡ ምክንያት ከሚፋጠጡ ይልቅ ይቀራረባሉ። አንዱ ሌላውን ከሚጠራጠረው ይልቅ መናበብና መደጋገፍ ገዢ የግንኙነት መገለጫ ይሆናል። ስለዚህ የዚህ ዓይነት ቁልፍ ባህርይ ይዘዋል እምንላቸው የግድቡ ገጽታዎች ምን ምን እንደሆኑ ለይቶ መመርመር ይገባል።

ለምሳሌ የኢትዮጵያ ጂኦፖለቲካዊ ወሳኝ ጥቅም ከሚገለጽባቸው የግድቡ ገጽታዎች ሁለቱን ለማየት እንሞክር። አንዱ  የግድቡ ግንባታ ፍጥነት ነው። ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የመሰረተ ድንጋይ በማኖር ከተጀመረ እነሆ አሁን አምስተኛውን ዓመቱን ለመድፈን ሁለት ወር ፈሪ ነው። ግንባታው መቸ ተጀምሮ መቸ ያልቃል የሚለው ጉዳይ የኢትዮጵያውታያንም የግብጻውያንም ስሜት ከተቃራኒ ምክንያት ቢሆንም እኩል ወጥሮ የያዘ ጉዳይ ነው። ይህ ሲጀመር ጀምሮ ከግንባታው ዕድገት ጋር እየጦዘ የተጓዘ ስሜት ነው። የጡዘቱ ንረት ከግንባታው ልዩ ልዩ እርከኖች ጋር  ከፍና ለጠቅ ሲል ተስተውሏል። የግድቡ ስራ ሲጀመር ግብጽ ውስጣዊ የፖለቲካ ትርምስ እያስተናገደች ነበረ። በዚያን ጊዜ የነበረውን የግብጽ የሽግግር ፓርላማ ህዝባዊ ዲፕሎማቶች ኢትዮጵያ ድረስ ልኮ ያቀረባቸው ሁለት ጥያቄዎች ነበሩ። ልዑካኑም አገራችን እየታመሰችና ሽግግር ስለሆነ እስክትረጋጋና ቋሚ መንግስት እስክታገኝ በሚል ነበር ጥያቄዎቹን ያቀረቡዋቸው። አንደኛው የኢትዮጵያ መንግስት ተቀብሎት ግን ገና በፓርላማ ጸድቆ ህግ እንዲሆን በአጀንዳ ተይዞ የነብረውን የኢንቴቤው ትብብራዊ ማዕቀፍ ሳያጸድቅ ግብጽ እስክትሸጋገር ድረስ ፓርላማው እንዲታገስ የሚል ሲሆን በተመሳሳይ ምክንያትም የተጀመረው የግድቡ ግንባታም ለተመሳሳይ ጊዜ የግንባታው ሂደት እንዲቆም ነበር። የልዑካን ቡዱኑን በጣም በሚያስደስት ወንድማዊ ሞቅታና አክብሮት ከመልካም ዲፕሎማሲያዊ መልእክት ጋር ያስተናገዱት ጠ/ሚ/ር መለስ ዜናዊ  ህጉን የማቆየት ጥያቄ ሲቀበሉ ግንባታውን የማቆየት ጥያቄ ግን ለድርድር አላቀረቡትም።

ግብጽ በተለያዩ ሰበቦች የግድቡ ግንባታ ለአፍታ ያህል ቆም እንዲልላት ያልጠየቀቸው ጊዜ የለም። ግድቡን ከማስቆም አንጻር በፕረዚዳንት ሙርሲ ጊዜ የታየው አስገራሚ ሁኔታ ደግሞ በኢትዮጵያ ላይ ያለሃፍረት የተሰነዘሩ የዛቻና ማስፈራርያ ግርግሮች ናቸው። የአባይን ተፈጥሯዊ መፋሰሻ መስመር ለግንባታው ስራ ሲባል ተጠልፏል የሚል ዜና በተሰማበት ጊዜ የግብጽ ምድር ተናጠች። ሙርሲ የሰበሰቡዋቸው የመንግስትና የፓርቲ ባለስልጣናት ግንባታውን ለማስተጓጎል በኢትዮጵያ ላይ ወታደራዊ እርምጃ ከመውሰድ እስከ ልዩ ልዩ የሴራዎች ስምሪት እንደሚካሄዱ በግላጭ ሲናገሩ ተደመጡ። አሁንም ድረስ ግድቡ በአካባቢያዊ ተፈጥሮና የሰዎች ደህንነት ላይ የሚኖረው ተጽ እኖ በምልአት ተጠንቶ እስኪታወቅ ድረስ “ግንባታውን ቆም አድርጉት” የሚል ውትወታ በየስብሰባ መድረኩና በግብጽ የሚድያ አውታሮች ያለመታከት የሚቀርብ ፈተና ነው።  ይህ ግን ያለመታከት መመከት ያለበት ነጥብ ነው። በዚህ በኩል እስከአሁን የታየ ድክመት የለም። የኢትዮጵያ መንግስት እዚችኛዋ ቁምነገር ላይ ያሳየው ጥንካሬ የሚደነቅና የሚበረታታ ነው። ቀደም ብየ እንደጠቀስኩት እሰከ አሁን የግድቡን የተፋጠነና ያልተቋረጠ ግንባታ ወደ መጨረሻው የጂኦፖለቲካዊ ልዕና የሚያደርስ

ሂደት መሆኑን ተገንዝቦ ለድርድርና ለማዘናጊያ ሴራዎች እንዳይጋለጥ አድርጓል። እርግጥ በገንዝብ ምክንያትና በሌሎች ተጨባጭ ከዓቅም በላይ የሆኑ ችግሮች ሊኖር የሚችለውን መጓተት ሌላ ጉዳይ ነው። የግድቡ ግንባታ ዘገየ ማለት ግን ኢትዮጵያ ከግብጽ ጋር ባላት ግንኙነትና ተዛማጅ ሁኔታዎች አንጻር ወደ አዲስ ምዕራፍ የምትሸጋገርበትን ፍጥነት ማዘግየት ማለት እንደሚሆን ሙሉ ግንዛቤ ማግኘት አለበት።

ሁለተኛው ከዚህ የጂኦፖለቲካዊ ቁምነገር አንጻር አያይዘን የምናየው ነጥብ የግድቡ አጠቃላይ ዓቅመ-ስፋትና ትልቀት ነው። ይህም ቅድም በአንደኛ ደረጃ የጠቀስነውን የግድቡ ጂኦፖለቲካዊ ቁመና የሚመለከት ነው። በዚህ ላይም ቢሆን አንዳችም ድርድር ሊፈቀድ አይገባም። ግብጾች ሁሌም የግድቡን መጠን አሳንሱት የሚል መደራደርያ ይዘው ለመቅረብ እንደሞከሩ፣ አሁንም ድረስ እንደሚሞክሩ ይሰማል። ቀደም ሲል ከላይ የጠቀስኩት በትልቁና 6250MW የማመንጨት ዓቅም ባለው ግዙፍ ታላቁ የህዳሴ ግድብ መጀመር ቁልፍ ምርጫ የሚሆንበትም አንዱ ምክንያት ከተባለው ጂኦፖለቲካዊ ጉልበት አኳያ ሲመዘን ነው። ለምሳሌ ግብጾች እንደ አማራጭ አቅርበውታል ተብሎ የሰማነው አንዱ የመደራደርያ ነጥብ የግድቡ መጠን አሁን ካለው ዕቅድ ዝቅ ብሎ በዚያ ምክንያት ኢትዮጵያ የምታጣውን የኃይል (power) መጠን በገንዘብ ተተምኖ ለኢትዮጵያ ማካካሻ እንዲሰጣት የሚያግባባ እንደነበር ነው። ብልጥ አቀራረቦች የሚከሰቱት በተለያየ ብልሃት ነው። አላማና ግባቸው ግን ሁሌም ከላይ ባነሳነው ቁምነገር ዙርያ እሚሽከረከር ነው። ግብጽ በዚህ አቀራረቧ ተሳክቶላት ተቀባይ ብታገኝ ለኢትዮጵያ እምትከፍለው ማካካሻ ክፍያ ኢኮኖሚያዊው ጥቅም የሚሸፍን እንጂ ዋናውን ጂኦፖለቲካዊውን ጉልበት ግን በተቃራኒው የሚቀንስ ነው። በእንደዚህ ዓይነት አቀራረብ ብንበለጥ ይህን ተዓምረኛ ግድብ የሚያስጨብጠንን የተጽእኖ ጉልበት በገዛ እጃችን ማስነጠቅ ይሆንብናል። ግብጽ ዘላለሚን በማስፈራራትና በብልጠት በኛ ኪሳራ ስትለማ የቆየች አገር ናት። ግብጽ ራሷ የመልማቷ ጉዳይ ሳይሆን ልማቷን ከኢትዮጵያ መቆርቆዝ ጋር አስተሳስራ የማየቷ ጉዳይ ነው ችግር የሆነው። ኢትዮጵያ ከዚህ ውትብትብ የግብጽ እንቅፋቶች በጥሰ እምትወጣበት ይህ ግድብ ሳይዘገይና ሳይሸራረፍ በፍጥነትና በምልአተ ቁመና ተሰርቶ እውን ሲሆን ነው። “ለድርድር አይቅረብ” ያልነው ወሳኝ ጥቅምም የሚረጋገጠው በዚህ መንገድ ነው።

### 3. <u>ተካካሽ አጀንዳዎች</u>

ሁለተኛው የህዳሴው ግድብ የፋይዳ ምሰሶው ኃይል ማመንጨቱ ነው። ይህ ገጽታ በባህርይው ኢኮኖሚያዊ በመሆኑ የሚካካስ (redressible) ነው። ይህም ገጽታ ቢሆን ግን መገለጫ አለው። ለምሳሌ ግድቡ በቶሎ ኃይል ማመንጨት እንዳለበት ይታወቃል። በፍጥነትና በሙሉ ዓቅም ኃይል ማመንጨት ይጀምር ዘንድ የግድቡ ግንባታ መጠናቀቅ ብቻ በቂ አይደለም። ግድቡ ሙሉ ለሙሉ ውኃ መሙላት አለበት። አንዱ የግብጽ ስጋትም ይህ ግዙፍ ግድብ ውኃ የሚሞላበት ፍጥነትና ሁናቴ በምን ያህል ጊዜ የሚለውንና በየወቅቶቹ ካለው የተለያየ የወንዙ የውኃ ይዘት መጠን ጋር ከማጣጣም ጋር የተያያዘ ነው። ይህም የግብጽ ስጋት ተገቢ ነው። ኢትዮጵያ ውኃውን በአጭር ጊዜ ግድቡን ለመሙላት ብትሞክር፣ ለምሳሌ ግድቡ እስኪሞላ ድረስ የሚፈሰውን ውኃ ሙሉበሙሉ ወደ ግድቡ ላስገባ ብትል ግድቡ ሞልቶ እስኪፈስ ድረስ ግብጽ ከዓባይ አንድም ጠብታ ውኃ ላይደርሳት ነው። ይህ ፈጽሞ ተፈላጊም ፍትሃዊም አይደለም። ስለዚህ ግብጽ በተራዘመ ሂደትና ከየወቅቱ ጋር በተጣጣመ ሁኔታ ግድቡ እንዲሞላ የምታቀርበው ጥያቄ ከትክክለኛ

ጉዳትና ስጋት የሚመነጩ በመሆኑ ጉዳቱንና ስጋቱን ለመቀነስ እንዲቻል ኢትዮጵያ ልታጤነው የሚገባ የድርድር ይዘት ነው። ኢትዮጵያ የነበራት ውጥን ግድቡ በ7 ዓመታት ውስጥ ተጠናቆ እንዲሞላ ነው።

ግብጽ የመሙያ ጊዜው ወደ 12 ዓመታት ሰፋ እንዲልላት መጠየቋን ሰምተናል። ይህ እውነት ከሆነ የግድ ግብጽ የጠየቀችውን ያህል ይሁን የሚል አቋም ባይኖረኝም ከጠየቀችው ጊዜ አጠር ያለ ወይም ከጠየቅችው የጊዜ መጠን ጋር የሚቀራረብ አማራጭ ለማስተናገድ የሚቻልበት መንገድ አለ። ኢትዮጵያ ለግድቡ የመሙያው ጊዜ ብላ ካቀደችው በላይ በረዘመ ሁኔታ ቢፈጸም ኪሳራው ኢኮኖሚያዊ ብቻ ነው የሚሆነው። በመሙያው ጊዜ መራዘም የሚከሰት ኢኮኖሚያዊ ኪሳራ ልክ ግብጽ ኢትዮጵያን በገንዘብ ብታካክስ ሁለቱም አሸናፊዎች የሚሆኑበት ሁኔታ ፈጠሩ ማለት ነው። ግብጽ ግድቡን በአጭር ጊዜ ለመሙላት ሲባል ልታጣው የምትችለውን ውኃ በዋጋ ቢተመን የትየሌሌ ነው። የጠየቀችውን የተራዘመ ሂደት በመቀበሏ ኢትዮጵያ ቶሎ በመሙላት ልታመርተው ከነበረው ኤሌክትሪሲቲ የሚቀርባትን ጥቅም ግብጽ በማካካስ ብትሸፍን አዋጭ ነው። ይኸኛው ሁለተኛው ዋና ጉዳይ በመሆኑ ልዩነቶችን በማቻቻልና ጉዳቶችን በመካፈል በገንቢ ድርድር የሚስተናገዱ ፋይዳዎች ያካተተ የግድቡ ገጽታ ነው። መፍትሄውም መተሳሰብና መግባባት ነው። ምክንያቱም ቅድም ከጠቀስነው የጂኦፖለቲካዊ ገጽታ ወጣ ያለና የአንዱ ወገን ተጠቃሚነት ለመጠበቅ ሌላኛው ትክሻ ላይ የሚያርፈውን ዕዳ በማካካስ የሚፈታ የኢኮኖሚ ጥቅም ጥያቄ ብቻ ስለሆነ።

## 4. <u>የጋራ አጀንዳዎች</u>

እላይ ካብራራሁዋቸው ሁለት ቀዳሚ ጉዳዮች በሶስተኛ ዘርፍነት የሚፈረጅ የግድቡ ገጽታ ሁላችንም በጋራ የምንጋራው ነው። ይህን ለመዘርዘርና በስፋት ለመተንተን አልሞክርም። ጉዳዩም ራሱን ችሎ ያን ያህል የሚያወዛግብና ስምምነት ላይ ለመድረስ የሚያስቸግሩ አጀንዳዎች የሚነሱበት ክፍል አይደለም። እዚህ ውስጥ ከግድቡ ግንባታ ጋር ተያይዘው የሚነሱ ቁምነገሮች ለምሳሌ ያህል ብጠቅስ “የግድቡ መሰራት በአካባቢው አቀማመጥና ተፈጥሮ ስለሚኖረው አሉታዊ ተጽእኖ፣ ግድቡ እጅግ ግዙፍ ከመሆኑ ጋር መወሰድ ስለሚኖርባቸው የደህንነት ጥንቃቄዎችና ተያያዥ ጉዳዮች” እና የመሳሰሉትን ማለቴ ነው። እነዚህ ሁኔታዎች በተመለከተ ቅድም ከላይ ከጠቀስናቸው የልዩነት አጀንዳዎች ጋር በማያያዝ ካልተወሳሰቡና ራሳቸውን ችለው እስከቀረቡ ድረስ ኢትዮጵያ፣ ሱዳንና ግብጽ በጉዳዮቹ ላይ አንድ ዓይነት ወይም ተቀራራቢ አቋሞ የማያራምዱበት ሁኔታ አይታየኝም። በዚህ ላይ አገሮቹ አቀማመጣቸው ግርጌ ወይም ራስጌ ከመሆናቸው ጋር በተነጻጻሪ ልዩነት አጋንነው የሚያቀርብዋቸው የጥንቃቄና የደህንነት ጉዳዮች ካሉም በምክንያትና በማስረጃ እንዲታዩ ማድረግ ነው። ከዚህ ውጭ ባለሙያዎችና ገለልተኝዝ ታዛቢዎች በሚያቀርቡዋቸው የጥናት ውጤቶችና የማስተካከያ ሃስቦች አገሮቹ ከየሁኔታቸውና ከእውነታዎቹ ጋር እያጣጣሙ ተግባብተው ሊሄዱበት የሚችሉ ብዙ ማጨቃጨቅ የሌለበት ሁኔታ ነው።

## 5. <u>አጠቃላይ ዕይታ</u>

የኢትዮጵያ መንግስት በዓባይ ጉዳይና በህዳሴው ግድብ ኢትዮጵያን ወክለው ለመደራደርና ለመስራት በሙያተኝነት ወይም በስልጣን ውክልና እየተሳተፉ ያሉት ኢትዮጵያውያን ይህንን እጅግ ውስብስብ የድርድር መድረክ በአሸናፊነት ለማለፍ በሚያደርጉት ጥረት የኢትዮጵያን የዘመናት ጥያቄ የሆነውንና

በግድቡ በኩል ሙሉ በሙሉ መረጋገጥ ያለበትን ጂኦፖለቲካዊ ጥቅም ፈጽሞ ባለማስነካት፣ የግብጽን እውነተኛ ቁልፍ ስጋቶች በማቃለል የኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች ቢቀንሱ ማካካሻ በመሻት፣ ለግድቡም ለሁላችንም ደህንነት ጥንቃቄ መደረግ ስለሚገባቸው ዝግጅቶች ደግሞ በጥናትና ማስረጃ ላይ በተመሰረቱ መግባባቶች እንዲከናወኑ በማስቻል የግርጌ አገሮቹን ሳይጎዱ ኢትዮጵያ የተሟላ ድል ተጎናጽፋ እንድትወጣ ማድረግ ይችላሉ የሚል እምነት አለኝ። በተጨማሪም ዜጎች የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ጅማሮ አምስተኛ አመቱን ለመቀበልና ለማክበር በምንዘጋጅበት ጊዜ ይህ ግድብ ለኢትዮጵያ ትልቁ የልማት ህዳሴ ማብሰርያ፣ የዲፕሎማሲ ጂኦፖለቲካዊ ጉልበት መጎናጸፍያ፣ የሰላምና የትሥሥር ጉርብትና ማጠናከርያ፣ ዋጋውም ከግምት በላይ መሆኑን ይገነዘባሉ የሚል እምነት አለኝ።

ከሁለት ዓመት በፊት የእንግሊዝኛው ጋዜጣ ዘሪፖርተር ላይ ጽሁፍ ያስነበቡን ፕሮፌሰር ሃጋይ ኤርሊክ ኢትዮጵያ አሁን ያለችበት ዘመንና መድረክ የተለየ እንደሆነ አመልክተዋል። እኚሁ በኢትዮጵያ ብዙ ምርምርና ጥናታዊ ፍተሻ ያደረጉ፣ መጻህፍትና ጽሁፎች ያሳተሙ፣ አሁን በቴልአቪቭ ዩኒቨርሲቲ የሚሰሩ ታዋቂው ምሁር ፕሮፌሰር ሃጋይ ኤርሊክ ግብጻውያን መላ ህይወታቸው በዓባይ ውኃ ላይ የተመሰረተ እንደመሆኑ ውኃውን በተመለከተ ከቁጥጥራቸው ውጪ በሆኑት እንቅስቃሴዎች ሁሌም መስጋታቸው ሊያስገርም እንደማይገባ ጠቅሰው፣ ከጥንት ጀምሮ ውኃው ላይ ሙሉና ብቸኛ ባለቤትነት እንዳላቸው መቁጠራቸው ግን አስገራሚ ነው ብለው እንደሚያምኑ አብራርተዋል። ፕሮፌሰር ሃጋይ ኤርሊክ እንዳሉት ግብጾች በ1971 ያጠናቀቁትን የአስዋን ሃይ ዳም ማንንም ሳያማክሩ የገነቡትም ይህንን "ናይል የግብጽ ብቻ" የሚለውን እምነታቸውን ከግብጻውያን ጭንቅላትና ከግብጽ መጻህፍት አልፎ መሬት ላይ ለማረጋገጥ ያለመ ሥራ ነው ይሉታል። ፕሮፌሰሩ አሁን ኢትዮጵያ ሌላ ግድብ እየገነባች ያለችው ግብጽ "የብቻችን" ለሚሉት የዓባይ ውኃ ሌላም ባለቤት እንዳለው እንዲያውቁና ከእውነት ጋር እንዲጋፈጡ የማንቂያ ደወል ሆኖ ያገለግላቸዋል ሲሉ ያክላሉ። ለግብጻውያን የማንቂያ ደወል የመሆኑን ያህል ለኢትዮጵያውያን ደግሞ የአዲስ ምዕራፍ ማብሰሪያ እንደሆነ ጠቅሰዋል። ኢትዮጵያ ከአንድ ሚልዬኔም የእንቅልፍና የቁልቁለት ጉዞ በኋላ በህዳሴው ግድብ ፊታውራሪነት የሚገለጽ ለመጀመርያ ጊዜ የትንሳኤ መንገድ እንደጀመረች ፕሮፌሰር ሃጋይ በግልጽ ቋንቋ ይነግሩናል።

የአገሮችና ህዝቦች ገናና ስልጣኔና ውድቀት በተመለከተ ብዙ የተሰነደና ያልተሰነደ ታሪክም አፈ ታሪክም አለ። ከፍታ ላይ ደርሰው፣ ወድቀው ተንኮታኩተው የቀሩ ገናና ስልጣኔዎች ብዙ ናቸው። ከወደቁበት ሽለቆ ተነስተውና አንሰራርተው እንደገና ወደ ክብር ቦታ የተመለሱ አገሮችና ህዝቦች ግን ጥቂቶች ናቸው። እስራኤል ከ"ነበረች" ወደ ፍጹም "የለችም" እንደገና ደግሞ ወደ "አለች" የተመለሰች በጠንካራ ዳግም የህልውና ትንሳኤ የምትገለጽ አገር ነች። የክርስቶስ ትንሳኤ ክዋኔም የተፈጸመባት አገር ናት። የትንሳኤዋ ምክንያትም የልጆችዋ እስራኤልን በመጠበቅና በመገንባት ያተኮረ ፍጹም አንድነትና ትብብር ነው። የኢትዮጵያውያን ቁርጠኝነትም ከዚያ ያነሰ መሆን የለበትም። ህልውናም ትልቅነትም የሚረጋገጡት በብቁ ሥራና በንቁ ትብብር ነው። የህዳሴው ግድብ ፍጻሜ ከኢኮኖሚያዊና ጂኦፖለቲካዊ ፋይዳው ባሻገር ወደፊት ሌሎች ይበልጥ ውስብስብ የሆኑት ትላልቅ የህዳሴ ስራዎች በአገራዊ መግባባትና አንድነት ለመፈጸም አዎንታዊ መንደርደርያና በራስ የመተማመን እርሾ የሚሰጠን ብርቅዬ ፕሮጀክት አድርገን እናየዋለን።